# የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
# በኮሎምበስ፣ ኦሃዮ በጠራው ስብሰባ የተላለፉ ውሳኔዎች

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በቅርብ ጊዜ በወያኔ/ኢህአዴግ የተፈጸመውን የድንበር መሬት አሳልፎ መስጠት ወንጀል በሚመለከት በኦሃዮ ስቴት በኮሎምበስ ከተማና አካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተገቢ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ቅዳሜ ነሐሴ 17 ቀን 2000 ዓ. ም. (Saturday, August 23, 2008) ከ 2:00pm እስከ 7:00pm ድረስ ታላቅ ስብሰባ አካሂዷል።

ተሰብሳቢው በኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ጠለቅ ያለ ታሪካዊ ግንዛቤ እንዲይዝ፣ ኢትዮጵያችን በአሁኑ ጊዜ የምትገኝበትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሕብረተሰባዊ ይዞታ ምንነት እንዲረዳ፤ የሃገራችንን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያለውን ሃላፊነት እንዲገነዘብ ለማስቻል የድንበር ኮሚቴው በነዚህ ጉዳዮች ላይ ከፍ ያለ እውቀት ያላቸውን ሁለት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በመጋበዝ ገለጻና ማብራሪያ እንዲሰጡ አድርጓል። እነርሱም፥

1. ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴ - የታሪክ፣ የፖለቲካል ሳይንስና የኢኮኖሚ ምሁር
2. አቶ ኦባንግ ሜቶ - የሰብአዊ መብት ታጋይና የአኝዋክ ፍትሕ ካውንስል መሥራችና መሪ ናቸው።

በተጨማሪም ዳር ድንበሩን ከልጅነት ጀምሮ በጥልቀት የሚያውቁ ሁለት የሃገር ሽማግሌዎች ሰፋ ያለ ገለጻ ሲያደርጉ፤ የድንበር ኮሚቴው አመራር አባልም የኮሚቴዉ አመሰራረት፤ እስካሁን ድረስ የፈጸማቸውን ክንውኖችና የወደፊት እቅዶቹን በተመለከተ በሰነዶችና በስዕሎች የተደገፉ መረጃዎችን በማቅረብ ሰፋትና ጥልቀት ባለዉ ሁኔታ ሰፊ ማብራሪያ ሰጠዋል።

ከገለጻው በኋላ በድንበሩ ጉዳይ እና ሌሎች የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ የሚመለከቱ በርካታ ጥያቄዎችን ለእንግዶቹና ለድንበር ኮሚቴው በማቅረብ በሰፋት ከተወያየን በኋላ፤ በቂ ግንዛቤዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በሙሉ ድምፅ ከታች የተዘረዘሩትን ውሳኔዎች አስተላልፈናል።

## ግንዛቤዎች፦

1. በቅርቡ ወያኔ/ኢህአዴግ ለሱዳን አሳልፎ የሰጠው የድንበር መሬት በሚመለከት በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ክህደት መሆኑን በመገንዘብ፤
2. አገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የግዛት አንድነቷንና ዳር ድንበሯን በሚያስደፍር፤ እንዲሁም ሕዝባችን በታሪክ፣ በባህል፣ በቋንቋና በጀግንነቱ ለአእላፍ ዓመታት የገነባውን ትስስርና አንድነት በሚሸረሽር አጥፊና ከሃዲ ሃይል ስር መውደቋን፤
3. አገራችን የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ሳትሆን በአንድ ድርጅት፣ በአንድ ግለሰብ አምባገነናዊ ስርዓት ተጨቁና እንደምትገኝ፤
4. አገራችን ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለችውን ሃብት በወግ ልትጠቀምበት የሚያስችል ስርዓት በማጣት ዘግናኝና አስከፊ በሆነ ድህነትና ረሃብ ወስጥ እንዳለች፤
5. ሕዝባችን በወያኔ/ኢህአዴግ ጸረ-ዴሞክራሲ ባህሪ፣ ጨካኝና አፋኝ ስርዓት ተወጥሮ በዓለም አቀፍ ሕጎች የተደነገጉትን መሰረታዊ የሰው ልጅ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ተነፍጎ እንደሚገኝ፣ .....ወዘተ ተገንዝበናል።

## ውሳኔዎች፦

1) ወያኔ/ኢ.ህአዴግ ከሱዳን መንግስት ጋር በምስጢር ባካሄደዉ ስምምነት ውሃ-ገብ ለም መሬትና ታሪካዊ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱን ሙሉ በሙሉ እናወግዛለን፤
2) ይህንን ስምምነት በመመርኮዝ የሱዳን ወራሪ ጦር የሃገራችንን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በመድፈር በወገኖቻችን ላይ ያካሄደውን ግድያ፣ አፈናና ከፍተኛ መፈናቀል፣ እንዲሁም በንብረት ላይ ያደረሰውን ዝርፊያና ቃጠሎ በጥብቅ እንኮንናለን፤
3) በእነዚህ አስከፊ ድርጊቶች የወያኔና የአልበሽር መንግሥታት ሙሉ በሙሉ ተጠያቂዎች መሆናቸውን እናስታውቃለን፤
4) ባለፉት 18 ዓመታት ወያኔ/ኢ.ህአዴግ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በማካሄድ ላይ ያለውን የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ረገጣ፣ ጭቆናና ጭፍጨፋ፣ የሃገር አንጡራ ሃብት ዘረፋ፣ ጸረ-ኢትዮጵያና ጸረ-የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ሴራ፣ አገር የማስገንጠልና የመሸጥ ከፍተኛ ወንጀል ያስከተለውን አሰቃቂ የሆነ ድህነት፣ ተደጋጋሚ አስከፊ ረሃብና ቀዛፊ ለሆኑ በሽታዎች መጋለጥ፣ ለስደት መዳረግና ለምሁራን መፍለስ ተጠያቂ እንደሆነ እናረጋግጣለን፤
5) በዚህ የተነሳ፣ የዚህ ጸረ-ኢትዮጵያ ቡድን በማንኛውም መንገድ ከስልጣን መወገድና ለታሪካዊ ፍርድ መቅረብ እንዳለበት እናምናለን፤
6) ፍትህ፣ ርትዕ፣ እኩልነትና የህግ የበላይነት የሰፈነባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መገንባት እንዳለባት አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን በማመን በየጎራው ተበታትነው የሚገኙ፥

- በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ጽኑ እምነት ያላቸው፤
- በሕዝባችን ታሪካዊ አንድነትና ወንድማማችነት እንከን ጥርጣሬ የሌላቸው፤
- በሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሰረታዊ እምነታቸው ያደረጉ፤

ተቀዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የሃይማኖት ተቋሞች እና ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በአንድ ላይ መሰባሰብና አብሮ መታገል የግድ መሆኑን በማመን፤ ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር አገራዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ግቡን ይመታል !
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
በኮሎምበስ፣ ኦሃዮ በጠራው ስብሰባ
የተገኘን ሃገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን

ነሐሴ 17 ቀን 2000 ዓ. ም. ( August 23, 2008 )
ኮሎምበስ፣ ኦሃዮ፣ አሜሪካ